# የዓለም ዓቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት/ 2016/2024

## የዓለም ብርሃን

**የዓለም ዓቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት፦ግንቦት 24-25**

## የመጽሐፍ ቅዱስ መልህቅ

የቪቫ የዓለም ዓቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት፦ :: በተለይም ልጆች ለልጆች እንዲጸልዩ ማድረግ. የ2016 መሪ ሃሳብ ከዮሐንስ 9 ቁጥር 5 ላይ የተወሰደው ነው። ኢየሱስ “በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ” ያለው ’የዓለም ብርሃን’ ነው’ የሚለው ቃል ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መልህቅ የዓይነ ስውሩ ፈውስ የተመዘገበበት የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ሙሉ ነው።



## የቪቫ አጀማመር

የቪቫ መስራች ፓትሪክ ማክዶናልድ በደቡብ አሜሪካ በጎዳና ላይ ለሚኖሩ ህጻናት ከአካባቢው ተልዕኮ ጋር ሲሰራ ስላየው ራዕይ ይናገራል። ፓትሪክ በምሽት የአንድ ሉል ሥዕል አይቷል ፣ እየተገረመ እያለ ሉሉ ሲሽከረከር በአንድ መንገድ "ጨለማ" ነበረበት፡፡ ከዚያም በድንገት፣ ትንሽ፣ደካማ እና ትርጉም፣ ትንሽ፣ደካማ እና ትርጉም የለሽ የሆኑ ጥቂት የብርሀን ቁንጮዎች ወጡ። ከዚያም ብዙ እና አካባቢን በሚሸፍኑ የብርሃን መገናኛዎች ውስጥ መገናኘት ጀመሩ። ድባቡ በእያንዳንዱ እርምጃ በሆነ መንገድ እየተለወጠ እና እየጨመረ እየጠነከረ ብሩህ እየሆነ መጣ። ፓትሪክ ራእዩ እግዚአብሔር ለጥያቄው የሰጠው ምላሽ እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ "እቅዱ ምንድን ነው? ጌታ ሆይ፣ የእነዚህን ሁሉ ልጆች ፍላጎት ማሟላት ይቻላል?" ራዕዩ ወደ ተግባር የተሸጋገሩ፣ ከአውታረ መረብ ጋር የተገናኙ እና ለጋራ ስታንዳርድ የታጠቁ የቅዱሳንን የጋራ  እንቅስቃሴ ያሳያል።



# የዓለም ዓቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት/ 2016/2024

## ብርሀን!

## መረጃዎች

ይህ የመረጃ ሰነድ ከዮሐንስ 9 ታሪክ ልጆች ሌሎችን በጸሎት እንዲመሩ የጊዜ ለመክፈት አራት ጭብጦችን በእንቅስቃሴዎች፣ የማስታወሻ ጥቅሶች እና ትግበራ ጥያቄዎች ያቀርባል ። በ2015 ቅዳሜና እሁድ የተሰጡ ምስክርነቶች ተካትተዋል። አኒሜሽናኖች (የምስል እንቅስቃሴዎች)፣ መዝሙሮች፣የፓወር ፖይንት አቀራረቦች አካቷል

**አራቱ ጭብጦች**

i) የእግዚአብሔር ሥራዎች - የመጀመሪያ ደረጃ ለሆኑ ልጆች ( ከ4 — 6 ) ዓመት ዕድሜ ክልል

ii) የእግዚአብሔር ተአምራት - ለትልልቅ ልጆች እና ለቅድመ- አሥራዎቹ ልጆች ( ከ8 — 12 ) እና ( ከ13 — 16 ) ዓመት ዕድሜ ክልል

iii) የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ - ለአዳጊዎች ( ከ16 — 19 ) ዓመት ዕድሜ ክልል

iv) በእግዚአብሔር ማመን - ለአዋቂ ወጣቶች እና ጎልማሶች



ልጆች በተለያዩ መንገዶች መጸለይ ይችላሉ፡ የሶስትዮሽ ጸሎትን በመፍጠር፣የጸሎት ዛፍ በመስራት፣ በፊኛዎች ላይ ጸሎቶችን በመጻፍ፣ በካርታዎች ላይ የጸሎት ማስታወሻዎችን በማስቀመጥ፣ወይም ቪዲዮዎችን በመጠቀም፣ በቀጥታ ዓለምአቀፍ ልውውጥ

## ለልጆች ጸሎት ሊሆኑ የሚችሉ ነጥቦች

i) ሰላም እና ፍቅር በቤቴ እና በቤተሰቤ ውስጥ።
ii) ስንታመም ወይም ስንጎዳ የምንበላው በቂ ምግብ፣ የምንጠጣው ንጹህ ውሃ፣ የምንለብሰው ልብስ እና የጤና አጠባበቅ።
iii) ሰላም እና በጎዳናዎች ላይ አመጽ እንዲቆም
iv) ለትምህርት፣ ትምህርት ቤት ገብቼ በደግ፣ አፍቃሪ አስተማሪዎች እንድማር።
v) ከጉልበተኞች እና አታላዮች እንድጠበቅ።
vi) አዋቂዎች ከአሁን በኋላ ሕፃናትን አሳንሰው እንዳይመለከቱ፣ ችላ እንዳይሉ ወይም እንዳይንቁ በልጆች ላይ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ።
vii) አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት በከተማችን ውስጥ የሕጻናትን ህይወት ለማሻሻል በፍቅርና በጋራ እንዲሰሩ።

# የዓለም ዓቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት/ 2016/2024

## 1፡ የእግዚአብሔር ሥራ

### የታሪክ መልህቅ - ዮሐንስ 9:1-12

አንድ ቀን ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲሄድ አንድ ሰው ሲለምን አዩ። ከመወለዱ ጀምሮ ዓይነ ስውር ነበር። ደቀ መዛሙርቱም። መምህር ሆይ፥ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እሱ ወይስ ወላጆቹ? ኢየሱስ የተሳሳተ ጥያቄ እንደጠየቁ ነገራቸው። ይልቁንም ይህ የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል ይገለጥ ዘንድ ነው አላቸው። ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- "እኔ በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።" ኢየሱስ መሬት ላይ ተፋ፣ ከአፈሩ ጋር ጥፍጥፍ አድርጎ በሰውየው አይን ላይ አደረገ። ሄዶ በሰሊሆም መጠመቂያ ልዩ ስፍራ እንዲታጠብ ነገረው። ሰውየው ሄደ። ታጠበ። ተአምር!ሆነ። አሁን ማየት ችሏል። ጎረቤቶቹ ባገኙት ጊዜ አንዳንዶች ይህ ተአምር መፈጸሙን ተጠራጠሩ። አይነስውሩን ለማኝ የሚመስል ሰው ነው አሉ።

## ተግባራት

i) የሸክላ ሐውልት፡ የሰውን የሸክላ ምስል ስራ (ማለትም ኢየሱስ) ይህ ዓይነ ስውሩ ሰው ያገኘውን ኢየሱስን ይወክላል። አሁን፣ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን መሆኑን ለማሳየት በራሱ ላይ
ብርሃን ወይም መስታወት ጨምር። ማየት የተሳነውን ሰው ለመወከል የሌላውን ሰው የሸክላ ሐውልት ሥራ።

ii) ዓይነ ስውር ጥበብ - ዐይን ተሸፍኖ ሳለ የአንድን ሰው ምስል በቤት አጠገብ ሳል። ምን ያህል ከባድ እንደሆነ አስተውል!
የትውስታ ጥቅስ
ዮሐ 9:5፡ "እኔ በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።

## የተግባር ስራ

የእግዚአብሔርን ሥራ ስለማየት ወደ ጸሎት ለማምራት እነዚህን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው።
i) መጥፎ ነገሮች ሲከሰቱ እግዚአብሔር እንዴት ገብቶ ሁኔታውን ሊለውጠው ይችላል? የእኛ ድርሻ ምንድን ነው?
ii) በቤተሰብህ/ሽ፣ በጓደኛህ/ሽ ቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት ወይም በአካባቢህ/ሽ ላይ ለውጥ አይተሃል? ለእነዚህ ተጨማሪ ለውጦች  መጸለይ እንችላለን?
iii) ሰውዬው ኢየሱስን አምኖ በገንዳው መታጠብ ከባድ ነበር (በአቅራቢያው ውኃ ሊጠቀም ይችል ነበር።) በአምላክ ስለመታመንስ ምን ማለት ይቻላል? ምናልባት የምንጠይቀው ለውጥ ብዙ ጊዜ ሊወስድ ይችላል? ምናልባት እኛም የራሳችንን ማድረግ ይኖርብን ይሆን?

ከፓትና፣ ህንድ የተሰጠ ምስክርነት፡ የዓለም የ 2015 ጸሎት እግዚአብሔር የሰጠንን ውብ ፍጥረት ለመጠበቅ ባለን ሀላፊነት ለልጆች ትልቅ ግንዛቤ አምጥቷል። ከመማሪያ ማእከል የሆነችው አንጃሊ አሁን አላስፈላጊ መብራቶችን እና የአየር ማቀዝቀዣዎችን ታጠፋለች፣ ቧንቧዎችን በመዝጋት ውሃ ትቆጠባለች፣ ችግኞችን ትተክላለች፣ አካባቢዋን በንጽህና ትጠብቃለች። እሷ አሁን የተፈጥሮ ተዋጊ ነች፣የእግዚአብሔር ፍጥረት ኩሩ ተንከባካቢ ነች፣እና እህቶቿ እና ጓደኞቿ ከእሷ ጋር እንዲቀሳቀሱ ሁልጊዜ ታበረታታለች።

## 2፡ የእግዚአብሔር ተአምራት

### የታሪክ መልህቅ - ዮሐንስ 9፡13-23

የፈወሰው ኢየሱስ መሆኑን ለጎረቤቶቹ ሲነግሩ ጎረቤቶቹ ዓይነ ስውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት። ዓይነ ስውሩ የሆነውን ነገር ገለጸ። ከእነዚህ መሪዎች መካከል አንዳንዶቹ ለፈውስ የሚሆን ጭቃ የተቦካው በሰንበት ቀን ነበር አሉ። በሰንበት ምንም ሥራ አይፈቀድም፣ስለዚህም ሰው የሆነው ኢየሱስ ኃጢአተኛ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ሲሆን አይችልም።ፈሪሳውያንም ሰውየው ልጃቸው መሆኑንና ዕውር ሆኖ መወለዱን እንዲያረጋግጡለት ወደ ሰውዬው ወላጆች ላኩ። ፈርተው ልጃቸው አሁን እንዴት ማየት እንደቻለ ጠየቁ። ዕድሜው ራሱን ለመግለጽ በቂ ነውና እሱኑ ጠይቁት አሉ።

## ተግባራት

i) የሚና ጨዋታ፡ ልጆቹ ታሪኩን በራሳቸው አንደበት እንዲሠሩ ያድርጉ። የተለያዩ ክፍሎችን በመውሰድ ህጻናት ሁለት ጊዜ እንዲሠሩት ማድረግ

ii) የብርሃን ማዕከሎች-የልጆች ቡድኖች የከተማቸውን ካርታ በትልቅ ካርቶን ላይ ይሳሉ። አብያተ ክርስቲያናት እና ትምህርት ቤቶች ያሉበትን ቦታ ምልክት ያድርጉ። በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እና ቤተ ክርስቲያን ላይ የ LED መብራቶችን አንድ ገመድ ያያይዙ። መብራቶችን ወደ ብልጭታ ይቀይሩ፣ለህጻናት የሚሰሩ እና ህጻናትን የሚያከብሩ የብርሃን ማዕከሎች ኔትወርክን ለመወከል እንደተሰራ አሳይ።

## የትውስታ ጥቅስ

ዮሐንስ 9፡15ለ፡- “ጭቃን በዓይኖቼ ላይ አደረገ” ሲል ሰውየው መለሰ፣ “ታጠብሁ አሁን አያለሁ” ሲል መለሰ።

**ተግባር**

የእግዚአብሔርን ተአምራት ስለማየት ወደ ጸሎት ለማምራት እነዚህን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው።

i) አንድን ሰው አንድ ነገር እንዲያደርግልን ስንጠይቅ መጠራጠር ምን ማለት ነው?

ii) ተአምር ምንድን ነው?

iii) አሁን ተአምር የት ያስፈልገናል?(ቤተሰብ ውስጥ፣ትምህርት ቤት ውስጥ፣ማህበረሰብ ውስጥ)

**በዛምቢያ ካሉ ልጆች የተሰጠ ምስክርነት፡**

"እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ እንደፈጠረ ተምሬአለሁ፤ እንዲሁም ሰዎች እንስሳትን የመውደድና የመንከባከብ ኃላፊነት እንደሰጣቸው ተምሬያለሁ።"

"እርስ በርሳችሁ ጸልዩ በእግዚአብሔርም ታመኑ። ማንኛውንም ነገር በእግዚአብሔር እጅ ማስገባት ትችላላችሁ፤ ችግር ውስጥ ብትሆኑም እግዚአብሔር ሊረዳችሁና ሊመራችሁ ይችላል።

"የእግዚአብሔርን ፍጥረት መንከባከብ አለብን። ሁሉም ልጆች ትምህርት ቤት ገብተው መማር አለባቸው።"

viva together for children

## 3፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ

### የታሪክ መልህቅ - ዮሐንስ 9:24-34

ፈሪሳውያንም የሰውዬውን ወላጆች ቃለ መጠይቅ ካደረጉ በኋላ ዓይነ ስውሩን እንደገና አስጠርተው:- “እውነት በመናገር ለእግዚአብሔር ክብርን ስጥ፤ ይህ ሰው (ኢየሱስ) ኃጢአተኛ መሆኑን እናውቃለን፤ እርሱም “ኃጢአተኛ መሆን ወይም አለመሆኑን እኔ አላውቅም” አይነ ስውር እንደነበርኩና አሁን እንዳየሁ አውቃለሁ። ፈሪሳውያን እንዴት እንደተፈወሰ ዳግመኛ ሲጠይቁት ሰውዬው ለምን ዳግመኛ መስማት እንደፈለጉ ገረመውና “እናንተ ደግሞ የእሱ ደቀ መዛሙርት መሆን ትፈልጋላችሁን?” አላቸው፡፡በዚህ ጊዜ ፈሪሳውያን ተሳደቡት። ስለ ኢየሱስም ከሰውየው ብዙ ምስክርነት ከሰሙ በኋላ ፈሪሳውያን:- አንተ ከመወለድህ በኃጢአት የተዘፈቅህ ሆነህ እንዴት ልትነግረን ደፈርህ እያሉ ከምኩራብ ወደ ውጭ ጣሉት።

## ተግባራት

i) ማን አለ? ልጆቹን በክብ ሰብስብ እና ከዚያ ዓይናቸውን እንዲሸፍኑ አድርግ። አንድ ልጅ
ወደ መሃል እንዲገባ በመምረጥ "ሂድ, በሰሊሆም መጠመቂያ ውስጥ ታጠብ" በለው፡፡
ይህ ልጅ እንደገና ክቡን ይቀላቀል። ልጆቹ ዓይናቸውን ገልጠው የኢየሱስን ድርሻ
ማን እንደተጫወተ ይገምቱ።

ii) የሚበላ ጭቃ - ቸኮሌት ኬክ ኩባያ መያዣ ውስጥ አስቀምጥ። አንድ ልጅ ሌላውን በማንኪያ
ይመግብ። አይናቸው ላይ ሳይሆን አፋቸው ላይ ያስቀመጡት፡፡

## የትውስታ ጥቅስ

ዮሐ 9:32-33፡ "ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው አይን የከፈተ ማንም ከቶ አልሰማም፤ ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ምንም ሲያደርግ ባልቻለም ነበር።"

ተግባር

የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስን ስለ ማዳመጥ ወደ ጸሎት ለማምራት በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

i) ለምንድነው አንዳንድ ልጆች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያውቁትና ሌሎች ግን
የማያውቁት?

ii) ስለ ኢየሱስ ማወቅ አስፈላጊ የሆኑት ሌሎች ነገሮች ምንድን ናቸው?

iii) ጸሎት ወደ ኢየሱስ የሚወስድ ከሆነ እኛ ደግሞ እንዴት ማዳመጥ እንችላለን? አሁን
ኢየሱስን ማዳመጥ ትችላለህ?

ከአስናት ታንዛኒያ የተሰጠ ምስክርነት፡ አስናት 15 አመቷ ሲሆን የወላጆቿ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ከእናቷ ጋር ትኖራለች። በ2014 በሳምንት መጨረሻ ፀሎት ጊዜ ቤተሰቧ እንደገና እንዲሰበሰቡ ፀለየች። በዚህ ዓመት "እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ለህዝቡ ስለሚያስብ በጣም አመሰግነዋለሁ። አባቴ እና እናቴ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው በመካከላቸው መግባባት እስኪፈጠር ድረስ ተለያይተው ነበር" አለችን። ባለፈው ዓመት መገባደጃ ላይ እርስ በርሳቸው መደወል ጀመሩ።ይህም ወላጆቼ እንደገና እንደሚሰባሰቡ ተስፋ ጫረብኝ፡፡ክብር ፀሎታችንን ለሚመልስ ለእግዚአብሔር ይሁን፡፡

## 4፡ በእግዚአብሔር ማመን

### የታሪክ መልህቅ - ዮሐንስ 9:35-41

ኢየሱስም ፈሪሳውያን (ቀድም ሲል ዕውር የነበረውን) ሰው ከምኵራብ እንዳወጡት ሰምቶ ባገኘውም ጊዜ፡ አንተ በሰው ልጅ ታምናለህን? ብሎ ጠየቀው::ጌታ ሆይ ማን ነው? ሰውየው ጠየቀ። "በእርሱ እንዳምን ንገረኝ" ኢየሱስም "አሁን አይተሃል ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው" አለ ከዚያም ሰውየው "ጌታ ሆይ አምናለሁ" ብሎ ሰገደለት። እንደ ፈሪሳውያን ያሉ ሰዎች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አይተው ሲቀበሉ አይችሉም:: ሲል ስለመንፈሳዊ ዕውርነት ተናገረ::

ያሳመኑት ይፈረድባቸዋል እና ጥፋተኛ ይሆናሉ።

## ተግባራት

i) መዝሙር - ወጣቶቹ ወይም ልጆች ቀላል መዝሙር እንዲፈጥሩ አድርግ።

ii) ኮላዥ(በሙጫ ወይም የሚለጠፍ) - ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያሳዩ ነገሮችን ከጨርቃ ጨርቅ፣ ባለቀለም ወረቀት ወይም ከቀለም ጋር አንድ ግዙፍ ኮላዥ ይስሩ። ይህንን ግድግዳ ላይ ያስተካክሉትና በጥቁር ጨርቅ ይሸፍኑት::ልጆች ስልክ ወይም ባትሪ ተጠቅመው ያበራሉ እና ፈሪሳውያን እንዳደረጉት "ምን? እኛ ደግሞ ዓይነ ስውር ነን?" ልብሱን አውልቀው፣ እና አሁን፣ መብራቶቹ ኢየሱስ ባደረጋቸው ነገሮች ላይ ሲያበሩ፣ "ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ አለ።'

## የትውስታ ጥቅስ

ዮሐንስ 9:38 ሰውየውም፡ ጌታ ሆይ አምናለሁ፡ አለ፡ ሰገደለትም።
ተግባራት
በአምላክ ላይስላለው እምነት ወደ ጸሎት ለማምራት እነዚህን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው።
i) እምነት ምንድን ነው?
ii) አንድ ሰው ዕውር እንደነበረው እና ከዚያም ማየት እንደቻለው ሰውዬ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እና ምን ማድረግ እንደሚችል ሲረዳ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዴት ይሆናል?
iii) ኢየሱስ በቤታችን፣ በጎዳናዎቻችን፣ በትምህርት ቤቶቻችን እና በኮሌጆቻችን ያለውን ሁኔታ መለወጥ የሚችል ይመስላችኋል? ጸሎትህን እና የሌሎችን ጸሎት እንደሚመልስ ለማመን የበለጠ እምነት ያስፈልግሃል? ለምን እንዲህ እንዲያደርግ አትጠይቀውም?

**በካምቦዲያ ካሉ ልጆች የተሰጠ ምስክርነት፡**
በጋራ መፀለይ በግል ከመፀለይ የበለጠ ኃይል እንዳለው ተናገሩ። ትልቅ ቡድንን እየመሩ ሲጸልዩ እንደ ንጉስ ወይም እንደ ንግስት እንደሚመስሉ ተናገሩ። የቤተክርስቲያን መሪዎች ለሚቀጥለው ትውልድ ልጆችን እንዲያሰለጥኑና ለተልዕኮው ለሚያስፈልገው ኃላፊነት እንዲዘጋጁ አሳስበዋል::

viva
together for children

# የዓለም ዓቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት/ 2016/2024

## የዓለም ብርሃን

የዓለም ዓቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት፦ግንቦት 24-25

**የመዝጊያ ጸሎት**

ኢየሱስ አንተ የዓለም ብርሃን ነህ። ከተወለደ ጀምሮ ማየት የማይችለውን ዕውር ሰው ፈውሰሃል፡ እውነተኛ ተአምር። የበኩሉን ማድረግ ነበረበት እና ወደ ሰሊሆም ለመታጠብ ሄደ። አንተን ማመን ነበረበት። አንተንም እንዳምን እርዳኝ ኢየሱስ። እንደ ፈሪሳውያን በአስተሳሰቤ እንዳልታወር እርዳኝ ነገር ግን በከተማችን በጣም ድሃ በሆኑ አካባቢዎች ያለውን ሁኔታ እንድትለውጥ እንድጠብቅ እርዳኝ። የታምራት ብርሃንህን በቤቴ፣ በጎዳናዬ እና በትምህርት ቤቴ ላይ አብራ። “ጌታ ሆይ እንደ ዓይነ ስውሩ እርግጠኛ እንድሆን አምናለሁ። ኢየሱስ እወድሃለሁ።

ዓለም አቀፍ የልጆች የፀሎት ሳምንት/ ዘመቻ በየአመቱ በግንቦት ወር የመጨረሻ ሳምንት ወይም በሰኔ ወር መጀመሪያ ሳይ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ጎልማሶችን እና ህጻናትን አንድ የሚያደርግ ዓለምአቀፍ እንቅስቃሴ ነው። በቪቫ የተደራጀው የበጎ አድራጎት ድርጅት የብዙ ልጆችን ህይወት ለመለወጥ እግዚአብሔር የሰጣቸውን እምቅ አቅም በዓለም ዙሪያ በ38 የማህበረሰብ አውታረ መረቦች ውስጥ ለማሚሳት ይሰራል።

www.worldweekendofprayer.com